# አዋጅ ቁጥር ________/2015

## የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ወደአገር በሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች እና አንዳንድ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን እጅግ በጣም ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ጭምር ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው እንዲያስገቡ መፍቀድ ተገቢ ባለመሆኑ፤

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልበት ማድረግ መንግሥት ለሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች የሚውል ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ስለታመነበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (ማሻሻያ) ቁጥር _____/2015” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2020 (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፤

1. ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (22) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (23)፤ (24) እና (25) ተጨምረው በነባሩ ከንዑስ አንቀጽ (23)-(34) የሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (26)-(37) ተደርገው ተሸጋሽገዋል፤

“23. “**ኤቲይል አልኮል**” ማለት ጥራቱ 80 ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ አልኮል ነው፤”

“24. “**አዲስ ተሽከርካሪ**” ማለት ከተመረተበት ዓመት ጀምሮ ከዚህ በታች ከተመለከተው በላይ አገልግሎት ያልሰጠ ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ. በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠም ሙሉ በሙሉ ተበትኖ ወደአገር የገባ ወይም በከፊል ተበትኖ ወደአገር የገባ ተሽከርካሪ፤

ለ. በጉምሩክ ታሪፍ በአንቀጽ 87.02፣ 87.03፣ 8704፣ 87.05 እና 87.11 የሚመደብ ሆኖ፤ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞ ወደአገር የገባ፤ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) በደረሰበት ጊዜ የተመረተበትን የዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ዕድሜው ከሶስት ዓመት የማያልፍ እና ከውጭ አገር እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) ድረስ የተነዳው ርቀት ከ4,000 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ “ለ” በታሪፍ አንቀጽ ተለይተው ከተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በሚቆጠር በአራት የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰ ነው፡፡”

“25. ***ያገለገለ ተሽከርካሪ”*** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (24) ለአዲስ ተሽከርካሪ በተሰጠው ትርጉም የማይሸፈን ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የአገልግሎት ዘመኑም ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ይጨምራል፡፡”

2. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፤

“2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተደነገገው መሰረት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 1 የተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በሰንጠረዡ በተመለከተው የማስከፈያ ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡”

3. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው ተራ ፊደል (ሀ) ተተክቷል፡

“1. (ሀ) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤”

4. ከአዋጁ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተጨምሯል፤

“5. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት የባንክ ፈቃድ አግኝተው ከማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ዕቃዎች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደአገር የሚገቡ ከሆነ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይደረጉባቸውም፡፡”

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ ከ______ቀን 2015 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ____ቀን 2015 ዓ.ም.

ሳህለወርቅ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

<u>ሠንጠረዥ ሁለት</u>

## ክፍል አንድ
## <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች</u>

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

1. አውሮፕላን በዓለምዐቀፍ ትራፊክ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ ተሳፋሪ መንገደኞች እና የአውሮፕላኑ ሠራተኞች በጉዞ ወቅት የሚጠቀሙባቸው በነፃ የሚሰጡ ዕቃዎች፣

2. የዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዟቸው በዲፕሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

3. በመንግሥት ጥሪ መሰረት በአደጋ የተጐዱ ሰዎችን ለመርዳ እንዲውሉ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች፣

4. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ወይም የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙዋቸው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

5. ከተሽከርካሪ በስተቀር ወደአገር የሚገቡ መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡ አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፤

## ክፍል ሁለት
## <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶች</u>

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፤

- ለዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች፤